# ግጥም በያይነቱ



በዘውገ ፋንታ
ታሕሳስ 2003

ባደኩበት ቤት፣
በፊት በስተጀርባው፣
ያለው ሰፊ መሬት፣
አነሰብኝ ምነው?

ባህር ምን ያደርጋል፣
ዋና ላማትችሉ፣
ታንኳስ ምን ይሰራል?
ሱዳን ኬንያ ጂቡቲ እያሉ!

ምፅዋና አሰብ፣
ሲስማዩ በርበራ፣
ይገባል አንተ ሕዝብ?
አትዛግ ኤርትራ፣
እያሉ ማሰብ?

እላለሁ ጠፋኝ፣
አገር ወገን አጣሁ፣
ያ አፈር እያለኝ፣
ምድር እሰኛለሁ።

በርሃ ይለምልም፣
ከጠፋ ደኑ፣
አውሬ አይገባውም፣
ተለውጧል ቀኑ።

ሲለወጥ ሲቀየር፣
ይወጣል ይወርዳል፣
ባህርም እንደ ምድር፣
ግልብጥብጦሽ ይላል።

ሰፊ ምድር አለን፣
የሚሉት አባቶች፣
ባህር አስጨነቀን፣
ጠፉና ሜዳዎች።

መዋያ የከብቶች፣
የሚታከት ለአይን፣
መሮጫ የጥጆች፣
ይሁን በቃ ይሁን፣
ካደረጉት ሰዎች።

ምነው በዛ ጎርፉ?
ውሃው ደፈረሰ፣
የወደቀው ዛፉ፣
ከስሩ ፈረሰ፣
ይኼ ከንቱ ክፉ፣
በሉ አገር ጣሰ፣
ይውረድ አትደግፉ።

ቦርከና በሽሎ፣
አሻቅበው ወጡ፣
ወንዝ ወጣ ኮብልሎ፣
ተከዜን መረጡ!
አባይን ሊያመልጡ።

በደረቁ መሬት፣
ሰከሩ ሳይጠጡ፣
ወንዙ እንደሰራዊት፣
ሰዎች እዩ ውጡ፣
አልቻሉም ወደፊት፣
መራመድ በቅጡ።

ምንጮቹም ሰክረዋል፣
ከሽለቆ ወጡ፣
ከተማ ገብተዋል፣
ባህር ስለአጡ።

እምቢ እያሉ ቁልቁል፣
ደረሱ አሉ ከታች፣
ሲወጡም ግልግል፣
እንቆይ ሳንሰለች፣
ቅዳሜ ቀርታለች።

ሲወርዱ በትግል፣
ሲወጡ በችግር፣
ስንቅ በይ አገልግል፣
ፈረደብሽ እግዜር፣
አረከሹሽ ይባል፣
አንቺ ድንግል ምድር!

መጡልሽ ወልቃይት፣
አርማጭሆ ዝም በል፣
እመቤት ያማራት፣
ልጅና ግልገል፣
ጠቅልሎ መጣላት።